# ስለ Fresh Bucks የተጠባባቂ ዝርዝር ማመልከቻ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የተጠባባቂ ዝርዝር ማመልከቻ

### የFresh Bucks የተጠባባቂ ዝርዝር ማመልከቻ ምንድን ነው?

የFresh Bucks የተጠባባቂ ዝርዝር ማመልከቻ በሲያትል ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች በወር $40 የሚሆን የFresh Bucks ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርቡበት ዕድል ነው። በሲያትል የሚኖሩ እና ለገቢ ብቁ የሆኑ ማመልከቻ የሚያቀርቡ ነዋሪዎች በተጠባባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣሉ እና በጀት ሲገኝ ስለ ምዝገባው ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

### ለFresh Bucks የተጠባባቂ ዝርዝር እንዴት ማመልከት እችላለው?

በበይነመረብ መስመር ላይ በFresh Bucks ድረ-ገጽ በኩል ማመልከት ይችላሉ። ማመልከቻው እስከ ወደፊት ክፍት ሆኖ ስለሚቆይ በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

### ለማመልከት ምን መረጃ ያስፈልገኛል?

የሚከተለው መረጃ እንደ የማመልከቻዎ አካል ይፈለጋል፦

- በቤተሰብዎ ውስጥ ስንት ሰው አለ?
- የቤተሰብዎ ገቢ ስንት ነው?
- የመኖሪያ አድራሻዎ የት ነው?

### ብቁ የሆኑት እነማን ናቸው?

የገቢ መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና በከተማው ወሰን ውስጥ የሚኖሩ የሲያትል ቤተሰቦች ለFresh Bucks ብቁ ናቸው። በከተማው ወሰን ውስጥ የሚኖሩ መሆንዎን ለማየት ይህን መሣሪያ ይጠቀሙ።

### የኔ ቤተሰብ ለበርካታ የFresh Bucks ጥቅማጥቅሞች ማመልከት ይችላል?

ጥቅማጥቅሞች ለአንድ ቤተሰብ አንድ ብቻ ሆነው ተገድበዋል። በቤትዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ቀድሞውኑ የተመዘገቡ ከሆነ፣ ተጨማሪ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

### የተመረጥኩ ከሆነ እንዴት ማወቅ እችላሉ?

ማመልከቻዎ ከተመረጠ፣ በቀጥታ በፖስታ እና በኢሜይል ማሳወቂያ ይደርስዎታል። በዚያን ጊዜ፣ የFresh Bucks ጥቅማጥቅሞችዎን መቀበል የሚጀምሩበትን ትክክለኛ የጊዜ ሰሌዳ እናሳውቅዎታለን።

### ካልተመረጥኩ፣ እንደገና ማመልከት ይኖርብኛል?

የለብዎትም። ማመልከቻዎ በመጀመሪያው ዙር ካልተመረጠ፣ ማመልከቻዎ ለወደፊት የምዝገባ ዕድሎች በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይቆያል፣ እና የእርስዎ እድል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይመጣል።

### የማመልከቻዬን ሁኔታ ማየት እችላለሁ?

የማመልከቻዎ ሁኔታ ከተቀየረ በፖስታ እና በኢሜይል እናሳውቅዎታለን። እንዲሁም የተለወጠ ነገር እንዳለ ለማወቅ በ206-256-5438 ወይም በ freshbucks@seattle.gov ሊያገኙን ይችላሉ።



Fresh Bucks በሲያትል ከተማ በጣፋጭ መጠጥ ግብር የተደገፈ ሲሆን
በሲያትል የዘላቂነት እና የአካባቢ ቢሮ የሚተዳደር ነው።

## በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እያለሁ ሁኔታዬ ቢቀየርስ?

የቤተሰብዎ ሁኔታ ከተቀየረ (ለምሳሌ አድራሻ፣ ገቢ፣ ወዘተ)፣ እባክዎ ማመልከቻዎን ለማሻሻል በ206-256-5438 ወይም freshbucks@seattle.gov ያግኙን።

## የተጠባባቂዎች ዝርዝር ያለው ለምንድነው?

የተጠባባቂ ዝርዝር ያለው Fresh Bucks ውስን የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ስላለው እና በአንድ ጊዜ ማገልገል የሚችለው የተወሰኑ ቤተሰቦችን ብቻ ስለሆነ ነው። የተጠባባቂ ዝርዝሩ ፕሮግራሙ የዘፈቀደ ምርጫ ሥርዓት በመጠቀም የፕሮግራሙን ፍላጎት በፍትሃዊነት እና በተገቢ ሁኔታ እንዲያስተዳድር ያስችለዋል።

# የማመልከቻ ምርጫ ሂደት

## የምርጫው ሂደት እንዴት ነው የሚሰራው?

የምርጫው ሂደት ለFresh Bucks ጥቅማጥቅሞች ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን በዘፈቀደ ይመርጣል። ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቤተሰቦች በምርጫው ውስጥ ተጨማሪ መግቢያዎች ይቀበላሉ፣ ይህም የመመረጥ እድላቸውን እንደሚከተለው ይጨምራል:-

- 1 ቅድሚያ የማግኛ መስፈርት የሚያሟሉ ከሆነ፣ ስምዎ 2 ጊዜ ይገባል።
- 2 ቅድሚያ የማግኛ መስፈርት የሚያሟሉ ከሆነ፣ ስምዎ 3 ጊዜ ይገባል፣ እያለ ይቀጥላል።
- ከመጀመሪያው የምዝገባ ጊዜ በኋላ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ የሚቀሩ ቤተሰቦች ለወደፊቱ ምርጫ ተጨማሪ መግቢያ ይቀበላሉ።

## ቅድሚያ የማግኛ መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

Fresh Bucks በምግብ ዋስትና እጦት፣ በኢኮኖሚ ችግር እና ከአመጋገብ ጋር በተያያዙ ሥር የሰደዱ በሽታዎች በጣም መከራ ለበዛባቸው ሰዎች በጤናማ የምግብ አቅርቦት ላይ ልዩነቶችን ለማስወገድ ያለመ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች እና የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች ለምግብ ዋስትና እጦት የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ቤተሰቦች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል:-

- የዝቅተኛ የቤተሰብ ገቢ ምድብ።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማይጠቀሙ ቤተሰቦች።
- የተጠባባቂ ዝርዝር ቆይታ:- ከመጀመሪያው የምዝገባ ጊዜ በኋላ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ የሚቆዩ ቤተሰቦች በቀጣይ የምርጫ ሂደቶች ውስጥ ተጨማሪ መግቢያ ይቀበላሉ።